በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን !!!

የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲርያን ቤተክርስቲያን

ተሞክሮ

አስፈላጊነት

- የቤተክርስቲያን የኩላዊነት (በሁሉ ያለች)ና አሐቲነት ባህሪ ስላላት
- ከታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጀምሮ በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል የልምድ ልውውጥ ይደረጋል
- በዚህ ዘመን በመላው ዓለም የምትገኝ አርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች እርስ በርሳችን የምንጋራቸው ብዙ የጋራ ክርስቲያናዊ እሴቶች፣ አብረን የምንጋፈጣቸውም ብዙ ተግዳሮች መኖራቸው
- በዘመናችን የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት ብዙ መልካም ነገሮችና ተግዳሮቶች መኖራቸው

አስፈላጊነት

- ከተለያዩ አብያተክርስቲያናት በጎ ተሞክሮዎች በመውሰድ የበለጠ ጥንካሬ ማግኘት እንድንችል
- በዘመናችን የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት ብዙ መልካም ተሞክሮዎችን ለመቅሰም
- የአብያተክርስቲያናት እርስ በርስ የመመካከር እና አንዱ ከሌላው የመማር እና የጋራ እሴቶችን የመጠበቅ ኦርቶዶክሳዊ መገለጫ አስጠብቆ ለማስቀጠል

ዓላማ እና ግብ

- **ዋና ዓላማ**
  - በህንድ ማላንካራ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለዉን መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እንዲሁም የገጠሟቸውን ተግዳሮቶች በመጠኑ መዳሰስ
- **ግብ**

- ከህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ልንማራቸው የሚገቡንን ተሞክሮዎች መቅሰም

ምን ይጠበቃል?

- በቀሰሙት ዕውቀት ራሳቸውንና ሌሎችን የሚመሩበት ጥበብ ቀስሞ ወደ ተግባር መቀየር
- በቀሰሙት ልምድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸዉን ከወቅታዊ እና መጻኢ ፈተናዎች በመታደግ ተልእኮዋን ለማሳካት እንድትችል ተገቢ ድርሻቸን መወጣት
- ቀደምት አባቶቻችን ለቤተ ክርስቲያናቸው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከተገነዘቡ በኋላ የእነርሱን አሠረ ፍኖት ተከትለው ቀጣይ አገልግሎታቸውን በትጋት እና በጽናት ያስኬዳሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ውስንነት

- በዚህ ጽሑፍ የተካተቱ አብዛኞቹ መረጃዎች በአካል በአገሪቱ ጉብኝት አድርገው ከነበሩ የተገኙ በመሆናቸው ለውይይት መነሻ እና የበለጠ እንዲያነቡ የሚያነቃቁ እንዲሆኑ እንጂ **ጥልቅ ሳይንሳዊ የጥናት ውጤቶች ተደርገው አይጠቀሱም::**

በእንተ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት

ቤተክርስቲያን አንዲት ናት!

- ቤተ ክርስቲያን **አንዲት ናት**፤ አጽንታ የምትኖረው እና የሰው ልጅ ሁሉ ይድንበት ዘንድ የምትሰብከው **ወንጌልም አንድ ነው**።
- ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች ስትሄድ ለአስተዳደር ያመች ዘንድ እና በልዩ ልዩ ታሪካዊ ምክንያቶች አስተዳደራቸው ልዩ ልዩ የሆነ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም **በመንፈሳዊ አቋሟ ግን ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት**።
- አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከመናፍቃን ሰዎች እና ከከሃዲያን ነገሥታት ጥቃት **በብዙ መሥዋዕትነት** ጠብቃ እስከዚህ ዘመን ቆይታለች፤ ወደፊትም ትኖራለች።
- ይህች አንዲት እና እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን “**ኦርቶዶክስ**” የሚል ታሪካዊ ቅጽል (መገለጫ) ተጨምሮላት ትጠራበታለች።

በእንተ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት (ቀጣይ)

- ይህ “ኦርቶዶክስ” የሚል ቅጽል በጽርእ (ግሪክ) ቋንቋ “**ቀጥ ያለ እምነት፣ ቀጥ ያለ አምልኮ**” የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ይህም ራሷን ከመናፍቃን ስህተት ጠብቃ የኖረች ርትዕት መሆኗን የሚገልጽ ነው።።
- በአጭሩ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማለት **የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን** ማለት ነው።።

ኦርቶዶክስ (አጎት) አብያተ ክርስቲያናት

- የአጎት አብያተክርስቲያናት የምንላቸው

  1. የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
  2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
  3. የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
  4. የህንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
  5. የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እና
  6. የኤርትራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።።

- እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት **ኦሪንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት** በመባል ይታወቃሉ።።

የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች

1. በመንፈሳዊ ሕይወትና የምሥጢራት ተሳትፎ
2. የክህነት አገልግሎት
3. ለሕጻናት እና ወጣቶች መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጠውን ትኩረት
4. መንፈሳዊ ተልዕኮን (Mission)
5. የልማት ተቋማትን
6. የዘመኑን የባሕል ወረራ

የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲርያን ቤተክርስቲያን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ በሆነው በቅዱስ ቶማስ ስብከት ላይ ተመስርታ እ. ኤ አ ከ52 ጀምሮ ክርስትናን በመቀበል በብዙ መከራና ውጣ ውረድ ውስጥ አልፋ

ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ከፐርሽያ

ጋር የቀረበ ግንኙነት ጀመረች።።ከፐርሽያኖች የሕንድ ቤተክርስቲያን የምሥራቅ ሲሪያን ቋንቋ እና የአምልኮ ሥርዓቶችን በመውረስ በሂደት የሲሪያን ክርስቲያኖች ተብለዋል።

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእስልምና መነሣትና የሕንድ የባሕር ዳርቻ አካባቢዎች በሙስሊሞች መወረር ምክንያት የሕንድ ቤተክርስቲያንን ከሌሎች የክርስቲያን ሀገሮች ተነጥላ ለመቆየት ተገደደች። ይሁንና ያሉትን አማራጮች በሙሉ በመጠቀም የነበረውን ሐዋርያዊ ትውፊት ተከትለው ጳጳሳትን ከምዕራብ እስያ ለማግኘት ጥረት ያደርጉ ነበር።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮማን ካቶሊኮች እና በ18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ፕሮቴስታንቶች ወደ ሕንድ እስኪመጡ ድረስ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲርያን ቤተክርስቲያን ከጥንት ከቅዱስ ቶማስ ክርስቲያኖች ጀምሮ እ.አ.አ እስከ 1657 ድረስ አንድነት ያላት እና የራሷ አገር በቀል ማንነት የነበራት ብቸኛዋ በሕንድ ምድር ያለች የክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ነበረች።

እ.ኤ.አ በ1599 በተደረገው ሲኖዶስ ስብሰባ አስገዳጅነት ቤተ ክርስቲያኗን ለ54 ዓመት በሮማ ካቶሊክ እንድትገዛ የተደረገው ጥረት የተሳካ ቢመስልም እ.አ.አ በ1653 በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ የቅዱስ ቶማስ ክርስቲያኖች በጋራ ሆነው ኮቺን አካባቢ ማታንቼሪ (Mattancherry) በተባለ ቤተ ክርስቲያን መስቀል ቆሞበት በነበረው ሥፍራ በመሰባሰብ በመስቀሉ ላይ ገመድ በማሰርና እያንዳንዱ የተሰበሰበ ክርስቲያን ገመዱን በመያዝ (በመንካት) ከሮማ ካቶሊክ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ላይኖራቸው በመማማል በኃይል የተጫናቸውን እና በሮም ካቶሊክ መገዛትን በመገልበጥ ነፃነታቸውን በማወጅ የኦሬንታል ቤተክርስቲያን መገለጫዎችን እና ሀገር በቀል ትውፊቶቻቸውን እንደገና በማደስ ወደቀደመ ማንነታቸው ተመልሰዋል።

በረጅም ጊዜ ሂደት ሕንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተንሰራፍተው የነበሩት የአንግሊካን ፕሮቴስታንቶች በሚሽነሪዎቻቸውና በኋላም በሂደት የተሐድሶ ሐሳባቸውን ተቀብለው ውስጥ ለውስጥ ሲሠሩ በነበሩ የሕንድ ቤተክርስቲያን ሰዎች አማካኝነት በደንብ የተቆጣጠሯቸውን አብያተ ክርስቲያናትና የቤተ ክርስቲያን ተቋማትን ለመገንጠል ተንቀሳቀሱ። የፍርድ ቤት ውሳኔውም ይህንን ጥማቸውን የሚያረካ ሆኖ በመወሰኑ የሕንድ ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፈለች።

- የሕንድ ቤተክርስቲያን የነበሩ ይዞታዎች፣ በኮታይም ከተማ የሚገኝና የተደራጀ ከፍተኛ ዘመናዊ ትምህርት ቤት፣ ለትምህርት ማስፋፊያ ተይዞ የነበረው ከፍተኛ ገንዘብ በተሐድሶ ስም ቤተ ክርስቲያኗን ለመክፈል አጀንዳ ይዘው ለነበሩት የፕሮቴስታንት ሚሽነሪዎች በፍርድ ቤት ተወሰነ።

እ.አ.አ ከ1893 በኋላ በተሐድሶ ስም አቀጣጥለውት የነበረውን የኦርቶዶክሳዊነትን ገጽታ ተላብሶ አስተምህሮውን ወደ ፕሮቴስታንታዊ እምነት የማንሸራተት ተልዕኮን በስፋት በመቀጠል ሰፊ መዋቅር ዘረጉ፡፡ እ.አ.አ በ1926 በተሐድሶ ስም በተለወጠ አስተምህሮ መሠረት መጽሐፈ ቅዳሴውን ከልሰው አሳተሙ፡፡ በዚህ ታደሰ በተባለው ቤተክርስቲያን ውስጥ እ.አ.አ 1952 ሌላ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተወልዶ ተግንጣይ ቡድኑ የሕንድ ቅዱስ ቶማስ ኤቫንጀሊካል ቤተክርስቲያን በሚል አዲስ ቤተክርስቲያን ተቋቋመ፡፡

ፈተና ጌጧ እስኪመስል ድረስ የሕንድ ቤተክርስቲያን ሌላም ፈተና አጋጥሟታል። የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተክርስቲያን እና የጃኮቢት ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተክርስቲያን እ.ኤ.አ በ52 በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በአንድ ቤተርስቲያን ጥላ ሥር የነበሩ የክርስያኖች ጎብረት ነበሩ። ይሁንና በአስተዳደር ጉዳይ በተፈጠረ ልዩነት ከዛሬ አንድ መቶ ዓመት በፊት ጀምሮ አብያተክርስቲያናትን እና ንብረቶቿን ተከፋፍለው ተለይተዋታል።

እመቤታችን ለሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የሰጠችም ሰበን የሚገኝበትን የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጨምሮ በብዙ ሺህ በሚቆጠሩ አጥቢያዎችና የቤተክርስቲያን ንብረቶች ላይ እኔ ይገባኛል ለእኔ በሚል ለመነጣጠቅ በሚደረግ ትግል ብዙ ፈተናዎችን አሳልፈዋል።

ልምድ አንድ

በመንፈሳዊ ሕይወትና የምሥጢራት ተሳትፎ

መንደርደሪያ

- በጥንቷ ቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት ቅዳሴ የሚቀደስበት ዋናው ምክንያት ምእመናን ከሥጋው እና ደሙ ይቀበሉ ዘንድ ስለሆነ ያስቀደሰ ሁሉ የመቁረብ መንፈሳዊ ግዴታ ነበረበት፡፡
- ለዚህም ነው በሥርዐተ ቅዳሴአችን መጀመሪያ ላይ፡-
  - ‹‹*ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅድሳተ ወኢተዐገሠ እስከይፈጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ ወኢተመጠወ እምቊርባን ይሰደድ እምቤተክርስቲያን* እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር…›› የምንለው፡፡
  - *ከሥጋውና ደሙ የማይቀበል ቢኖር ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ/ይራቅ፤ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና*
- ዳሩ ይህንን የምንለው በግእዙ ስለሆነ እና አብዛኛው ምእመንም ምን እያለ እንደሆነ እንኳን በወጉ ስለማይረዳ በራሱ ላይ እየዳኘ ነገር ግን በቸርነቱ ይኖራል፡፡

በሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን

- የጥንቱ ሥርዓት የነበረ የምሥጢራት ተሳትፎ ትውፊት ዛሬም ድረስ ሙሉ በሙሉ እየተተገበረ ይገኛል።
- ክርስቲያኖች ከዕለተ ሰንበት ቅዳሴ በፊት ንስሐ አባታቸውን ያገኛሉ። የአንድ ቤተሰብ አባላት ሁሉም በጋራ ይቆርባሉ።





በኢትዮጵያስ?

- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ ከደረሱባት ፈተናዎች የተነሣ ይህ የምሥጢራት ተሳትፎ ሕይወቷ እየተመናመነ ቢመጣም ጥንቱን ግን (በቅርቡ በ15ኛው መ/ክ/ዘ፣ በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን እንኳን) ላስቀደሰው ሁሉ

‹‹*የሚቻለው ሥጋውን ደሙን ይቀበል፤ ከአቅም በላይ የሆነ እክል ገጥሞት መቀበል ባይቻለው ግን ተዓምሯን ሰምቶ ወደ ቤቱ ይሂድ*...››

የሚል አዋጅ የተቀመጠው ያን ጊዜ እንዳሁኑ ፈጽሞ አለመመናመኑን ከመጠቆሙም በላይ ለክርስቲያኖች ይህ **የምሥጢራት ተሳትፎ ለድርድር የማይቀርብ ጉዳይ** እንዳልሆነ ለመጠቆም ጭምር ነው።

ልምድ ሁለት

የክህነት አገልግሎት በተመለከተ

የክህነት አገልግሎት በአጎት አብያተክርስቲያናት

- የክህነት ቅብብሎሽ አርቶዶክሳዊያን አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያዊ መሆናቸውን ከሚገልጡባቸው የክርስትና ምሥጢራት አንዱ ነው::
  - ማንኛቸውም አርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በምሥጢረ ክህነት ያምናሉ፤
  - የክህነት ተዋረዳቸውንም ከሐዋርያተ ጀምረው ይቆጥራሉ::
- ምሥጢረ ክህነት ታላቅ መንፈሳዊ የአልግሎት ጸጋ ነው::
- በአርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ከፓትርያርክ ጀምሮ በየደረጃው ያለው ካህን ምዕመናንን የመጠበቅ ታላቅ የእረኝነት አደራ አለበት::

የክህነት አገልግሎት በአጎት አብያተክርስቲያናት (ቀጣይ)

- ከእግዚአብሔር የሚሰጠው ጸጋ እንዳለ ሆኖ የዘመናችን ካህን የተሰጠውን አደራ በአግባቡ እንዲወጣ እና በጎችን በአግባቡ ጠብቆ ለመንግሥተ ሰማያት እንዲያበቃ **ዘመኑን የዋጀ እና ምዕመናን በዘመናችን የሚያጋጥማቸውን ፈተና የሚረዳ** ሊሆን ይገባል።
- በተጨማሪም **የዘመኑን ቋንቋ እና አስተሳሰብ** አውቆ ማስተማር የሚችል ቢሆን ውጤታማ ይሆናል።

የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት


- የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን **ታላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ** ካህናት ባለቤት ናት።
- ቤተ ክርስቲያኒቷ ተበታትነው ያሉ ምዕመናኗን **በትጉህ ካህናቷ** ትጠብቃለች።
- በዚህች ቤተ ክርስቲያን **ዘመናዊውን ዓለም ከኦርቶዶክሳዊ የክርስትና አስተምህሮ አንጻር መመልከት የሚችሉ** እና በጎችን ከዘመኑ ፈተናዎች መጠበቅ የሚችሉ ሊቃውንት አበው ይገኙባታል።



ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጳውሎስ ማር ጎርጎርዮስ

- በቅርቡ ያረፉት በሕንድ የዋና ከተማዋ (New Delhi) ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት **አቡነ ጳውሎስ ማር ጎርጎርዮስ** ትልቅ ማሳያ ናቸው፡፡
- እኒህ አባት ሳይንቲስት የነበሩ ሊቀ ጳጳስ ናቸው፡፡
- ታላቅ የሥነመለኮትና የሥነጽሑፍ ሰው ነበሩ፡፡ ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡
- የሳይንስ መንገዶችን እና ዘዴዎችን (Scientific Methods) በኦርቶዶክሳዊ ክርስትና መነጸር መርምረው እስከመተቸት የደረሱ እና በዓለማቀፍ የሳይንቲስቶች ጉባኤ እንኳ በክብር የሚጋበዙ አባት ነበሩ፡፡





የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት (ቀጣይ)

- የህንድ ቤተ ክርስቲያን **የጠለቀ የሥነ መለኮት ዕውቀት** ባላቸው ካህናቶቿ ትታወቃለች፡፡
- እነዚህ አበው በሀገራችን **የሥነ መለኮት ት/ቤቶች** ሳይቀር ለረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ አላቸው፡፡
- በሀገራችን ካስተማሩ ሊቃውንቶቿ መካከል
  - V.C. Samuel (‘The Council of Chalcedon Re-examined’ በሚል የሚታወቀው መጽሐፍ ደራሲ)፣
- Fr. Jossey (በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያስተማሩ ምስጉን መምህር) የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡
- **አቡነ ዲዮስቆሮስ** (1987 – 1989 ዓ.ም) በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አስተምረዋል



የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት (ቀጣይ)

- የቤተክርስቲያኒቱን ካህናትና ጳጳሳት ከመመረጣቸው በፊት ምዕመናን ሀሳብ የሚሰጡበት መንገድ (መድረክ) አለ
- በተለይም ጳጳትን ለመምረጥ የሚከተሉት መንገድ **ፓርላመንታል** በመንፈሳዊ ምርጫ ሂደት ከእህት አብያተክርስትያናት አንፃር ትልቁ የዲሞክራሲ ስርዓት አስብሎታል፡፡
- በየአጥቢያዉ ያሉ ክህናትን የክፍሉ ጳጳስ የሚመደብ ሲሆን አንድ ካህን አንድ አጥቢያ ላይ ከሶስት ዓመት በላይ ማገልገል አይችልም፡፡
- ካህናቱ ሁለት ዓመት የአገልግሎት ጊዜያቸዉን በአንድ አጥብያ ላይ እንደጨረሱ በቀጣይ የሚመደቡበት ቦታ ተነግሯቸዉ ራሳቸዉን እያዘጋጁ ይቆያሉ፡፡
- ይህም በሀገረስብከቱ በሚታተም ወርሃዊ መጽሔት አማካይነት ለሁሉም ምዕመናን ይነገራል፡፡

የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት (ቀጣይ)

ወደ ሴሚናሪ እንዴት ይገባል

- በማላንካራ ኦርቶዶክስ ሴሪያን ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ወደ ሴሚናሪ/ቲዎሎጂ/ ኮሌጅ ለመግባት የሚፈልግ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያለፈና ቢያንስ **በሴኩላሩ የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ** ሊኖረዉ ይገባል።
- ከዚህም ባሻገር በሚመደብበት ሀገረስብከት በመሄድ ከ 8-10 ወር ዝግጅት ሥራ እየሰራና ሀገረስብከቱን እያገለገለ ይቆይና ከሊቀጳጳሱ የይሁንታ ድጋፍ ሲያገኝ ለመግቢያ ፈተና ይቀመጣል።

የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት (ቀጣይ)



- ፈተናዉን ካለፈ ለአምስት ዓመት የሴሚናሪ ትምህርት አጠናቆ ይመረቃል።
  - ከዚህ በኃላ አግብቶ አልያም መንኩሶ ወይ ቄስ አልያም መነኩሴ በመሆን በሀገረስብከቱ ባሉ አጥቢያ ለአገልግሎት ይመደባል።
- በአጥቢያ ላይ ያለው ካህን ዕለት ተዕለት ከሚያደርገዉ የመቅደስ አገልግሎት ባሻገር በተመደበለት መርሐግብር መሰረት በየመንደሩ በሚደረጉ የምዕመናን የፀሎትና ትምህርት መርሐግብር ላይ ላይ ይገኛል።



የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትወስደው ልምድ

- ከላይ ለምሳሌ ካየናቸው አብያተ ክርስቲያናት **የምንወስደው ልምድ**

1. በዩኒቨርሲቲ ያለፉ እና ዘመናዊውን ዕውቀት ከጥልቅ ሐይማኖታዊ እውቀት ጋር አገናዝበው የያዙ ምሁራን እንደሚያስፈልጓት ነው::
2. የዘመናዊውን ዓለም ፈተና የተረዱ እና የሚፈልገውን መሥዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ ካህናት ከአዲሱ ትውልድ መካከል መውጣት እንዳለባቸው እንረዳለን::
3. በተለይ ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች/የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ንስሃ አባቶች በመሆን የሚያገለግሉት ካህናት መንፈሳዊውን እውቀት ከአስኳላው አጣምረው የያዙ ቢሆኑ እጅግ መልካም ውጤት ባፈራን ነበር::

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትመሰደው ልምድ

4አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚስተዋለው ችግር በከፊል “ሃይማኖት ጠል” የነበረው ሶሻሊስት አስተሳሰብ በሃገራችን ላይ የፈጠረው መሆኑን ተገንዝበን የተማረው እና አዲሱ ትውልድ ቤተ ክርስቲያኑን በክህነት በማገልገል እንደ የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የክህነት አገልግሎት ለውጥ ለማምጣት መጣር ይጠበቅብናል።

- 5ከሁሉም በላይ ይህ ተስፋ ያለው ቤተ ክርስቲያን እያስተማረችው ካለው የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና የግቢ ጉባኤ ትውልድ በኩል ነው።

ልምድ ሦስት

ለሕጻናት እና ወጣቶች መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጠውን ትኩረት በተመለከተ

- “A Church without Youth is a Church without a future. Moreover, Youth without a Church is Youth without a future. ወጣቶች የሌሏት ቤተ ክርስቲያን ርእይ/ወደፊት ቀጣይነት የላትም ፣ እንደዚሁ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን በአፍአ የሆነ (የተለየ) ወጣት ፍጻሜው አያምርም” የሚለው ወርቃማ ንግግር በቅርቡ ያረፉት የግብጽ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የፖፕ ሺኖዳ 3ኛ ነው።።



የህንድ ማላንካራ ሴሪያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን

ከቤተ ክርስቲያኒቱ ከምንማራቸው ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹ፡-

1. በቤተክርስትያኒቱ ሊቃነጳጳስት፣ ሊቃውንትና ምሁራን አማካይነት ከነርሰሪ (ቅድመ አንደኛ ደረጃ) አንስቶ እስከ 12ኛ ክፍል በየደረጃው ተከፋፈለ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የትምህርት ሥርዓት አዘጋጅታ ታስተምራለች፡፡
2. ህፃናትን በመንፈሳዊ ትምህርት እና በሥነ ምግባር ለመቅረፅ እንዲቻል አብዛኞቱ የሰንበት ትምህርት ቤት **አስተማሪዎች በእድሜ ትልልቅ** የሆኑ ሲሆን **በአስኳላ ትምህርታቸውም እስከ ፕሮፌሰርነት** መዓረግ የደረሱም ይገኙበታል፡፡





የሕንድ ማላንካራ ሲሪያን ኦርቶ ዶክስ ቤተክርስትያን (ቀጣይ)

- ህፃናቱን ከመንፈሳዊ ትምህርት ባሻገር በአስኳላውና በማህበራዊ ተሳትፎ ላይ ጠንካራ እንዲሆኑ የተለያ ሥራዎችን የሚያከናዉኑ ሲሆን ከነዚህ መካከል፡-
  - **የቋንቋ ችሎታቸውን** እንዲያዳብሩ የእንግሊዘኛ፣የማሊያለም (የቤተክርስቲያኒቱ መገልገያ ቋንቋ) ማስተማር፤
  - ህጻናቱ ያላቸውን **ልዩ ተሰጦ** (ስዕል መሳል፣ግጥም መጻፍ፣ ሙዚቃ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወዘተ) የሚለማመዱበትና የሚሸለሙበት ስርዓት መኖሩ፤
  - ህጻናቱ በቤተክርስትኛን የቅዳሴ ስርዓት ላይ **መንፈሳዊ ጹሑፍ እንዲያነቡ**፣ ልዩ ልዩ መርሐ ግብራት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤
  - የህጻናቱን **የልደት ቀን** በሰ/ት/ ቤት ማክበር፤
  - **የወላጆች እና የህጻናት የጋር መርሐ ግብር** መኖሩ (ምሳሌ መዝሙር በጋራ ማቅረብ)።

የሕንድ ማላንካራ ሲሪያን ኦርቶ ዶክስ ቤተክርስትያን (ቀጣይ)

- ወጣቶቹን በሥርዓተ ትምህርቱ በሰንበት ትምህርት ቤት እንዲማሩ ከማደረጉ ባሻገር የተለያዩ የአገልግሎት መዋቅሮች እንዲሳተፉ በማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እየተደረገ ይገኛል::
- የቤተክርስትያኒቱን ወጣቶችን ሙሉ በሙሉ ለመያዝ **እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል በስርዓት የተከፋፈለ መንፈሳዊ ትምህርት** የሚማሩ ሲሆን ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሲቀላቀሉ በአንጋፋው እና በሊቃነ ጳጳሳት የሚመራው **የማር ጎርጎርዮስ የክርስቲያን ተማሪዎች ህብረትን (MGOCSM)** ይቀላቀላሉ::
- በዚህ መልኩ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡት ወጣቶች **በMGOCSM (የእኛው ግቢ ጉባኤ ዓይነት ነው)** እንዲሳተፉ መደረጉ ለነገ የቤተክርስቲያኗ አገልግሎትን ከማገዝ ባሻገር **ፓትርያርኮችን፣ ጳጳሳትን፣ መነኮሳትን እና ካህናትን** ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል::

የሕንድ ማላንካራ ሴሪያን ኦርቶ ዶክስ ቤተክርስትያን (ቀጣይ)

- ከደረሰባቸው ታሪካዊ ፈተና በመማር ጊዜውን ለመዋጀት በሁለተናዊ (Integrity) መንገድ፣ ይልቁንም በወጣቶች ላይ አድርገው መንቀሳቀስ መቻላቸው፤
- ወጣቶች የነገ የቤተክርስቲያኗ ተረካቢ መሆናቸውን በማወቅ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለቤተክርስቲያን መስጠት መቻላቸው፤
- ወጣቶቹ በትምህርታቸው እንዲበረቱ ባመጡት ውጤት ይሸልማሉ። ይህ ሲደረግ ደግሞ በመንፈሳዊው እና በቀለም ትምህርቱ ብቻ ሳይሆን በየአጥቢያው የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችን በማዘጋጀት ማወዳደር እና አሸናፊውን መሸለማቸው እርስ በርስ እንዲተዋወቁና የአጥቢያ አብያተክርስትያና ቅርርብ ለማጠናከር ረድቷታል።

የሕንድ ማላንካራ ሴሪያን ኦርቶ ዶክስ ቤተክርስትያን (ቀጣይ)

- የመንፈሳዊ ፕሮግራሞች ውድድሮችና የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- የሁለተኛ ደረጃ እና የኮሌጅ (ዩኒቨርሲቲ) ተማሪዎችን በአጥቢያ ደረጃ ከሚሳተፉበት አገልግሎት ባሻገር በክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ወይም በቤተክርስቲያኒቱ አስተባዳደር የሚመራ ሴሚናር፣ ኮንፍረንስ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡
- **በዚህም ፕሮግራም ላይ ከመንፈሳዊው መርሐግብር ባሻገር፡-**
  - የሳይኮሎጂ ምክር
  - በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ ስልጠናና ሜንተሪንግ (መቅረጽ)
  - በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቤተክርስቲያኒቱ ታላላቅ ሰዎች የማነቃቂያ ንግግር

የሕንድ ማላንካራ ሲሪያን ኦርቶ ዶክስ ቤተክርስትያን (ቀጣይ)

ቤተክርስቲያኒቱ ምን ተጠቀመች?

- በቤተክርስቲያኒቷ **አጠቃላይ የአገልግሎት፣ የልማት እንቅስቃሴ** ላይ በሙሉ ኃላፊነት እና ባለቤትነት መንቀሳቀስ መቻላቸው፤
- ወጣቶች **ለምስጢራት ቅርብ መሆናቸው** እና **በምክረ ካህን** በየጊዜው መመራታቸው፤
- ወጣቶች በተማሩት የአስኳላ ትምህርት ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት እና የትርፍ ጊዜያቸውንም በመጠቀም **የቤተክርስቲያኗን አገልግሎት በቴክኖሎጂ ውጤት እንዲደገፉ** ማድረጋቸው
- እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን **የራሱ Website መኖሩ** የማኅበራዊ ሚዲያን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ማድረጋቸው
- **በውጪው ዓለም የሚገኙ የቤተክርስቲያኒቷ ልጆች** ባሉበት ቦታ አገልግሎቱን ከማፋጠን ባሻገር በሀገረ ሕንድ የሚገኙ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች በሚያደርጉት **ዓመታዊ ልዩ መንፈሳዊ መርሐግብር ላይ ትኩረት ሰጥተው ተካፋይ ለመሆን መምጣታቸው** ያለውን የመንፈስ አንድነትና የሐዋርያዊ ተልእኮን የሚያሣይ ነው::

- መልካም እረኞች (ዲያቆናትን፣ ካህናትንና ጳጳሳትን) አጣን ብለን **ከምንቆዝም** የምንፈልገውን ዓይነት ጳጳስና ፓትርያርክ የሚያፈሩልን ሊቀ ዲያቆናት ሀቢብ ጊዮርጊስን የመሰሉ ወጣቶችን **ከሰ/ት/ቤት እና/ወይም ከግቢ ጉባኤያት ማፍራት** ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይሻላታል!
- በሰ/ት/ቤትና በግቢ ጉባኤያት ያሉ ተማሪዎችም አሁን ላይ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የሚታዩትን የአመራር እና ሥነ ምግባር ብልሹነቶችን እያዩ ከመንቀፍ ይልቅ **ራሳቸውን በትምህርት አብቅተው፣ በተገቢው አርቶዶክሳዊ ሕይወትና አቋም ለተተኪነት ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል!**

ልምድ አራት

መንፈሳዊ ተልዕኮን

(Mission)

የሀገረ ማለንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች የቤ/ክ መሠረቶች የአገልግሎት መርሐዎች

- **ሀ) ጸሎት**
  - “we used to spend the whole night in prayers and then in the morning we walk for miles to go to the mountain where Fr. Mina the Hermit (Ordained as Pope Kyrillos VI later) to pray the Divine Liturgy with him.

    ሌሊቱን ሙሉ በጸሎት ስንተጋ ካደርን በኋላ ሲነጋ ደግሞ ከባህታዊው አባ ሚናስ ጋር በአንድነት በጸሎተ ቅዳሴ ልንሳተፍ ረጅም ጉዞ ወደ ተራራው እንጓዝ ነበር” (*H.G. Bishop Mina Ava Mina)*
- **ለ) ቁርጠኝነት**
  - “Those persons devoted all their lives to God … They spent every minute of their time in the ministry … They considered the spiritual ministry as their main work and other worldly affairs as secondary፤

    መላ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ሰዎች…የጊዜአቸውን እያንዳንዷን ደቂቃ በአገልግሎት ላይ ያሳልፉ…መንፈሳዊ አገልግሎትንም እንደ ዋና ሥራቸው ቆጥረው ሌሎች ዓለማዊ ጉዳዮቻቸውን እንደ ሁለተኛ ጉዳይ /ተጨማሪ/ ያደርጋሉ፡፡ (*H.H. Pope Shenouda III,)*

ቤ/ክ ወጣቶች የአገልግሎት መርሐዎች (ቀጣይ)

- **ሐ) ራስን መስጠት፡-**
  - “There is a need for full-time dedicated servants. We need to encourage youth to devote one year after graduation to serve in evangelism

    የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች መኖራቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ወጣቶችንም ከምረቃቸው በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል በሐዋርያዊነት ለማገልገል እንዲወስኑ ልናበረታታቸው ይገባል፡፡”

እኛ የምንቀስመው ልምድ

ለምሳሌ ያህል፡-

1. **የተደራጀና የተጠናከረ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ይሰጣሉ**
   - በወጣቶቻቸው አማካይነት የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀጣይነት እንደሚረጋገጥም አጥብቀው ያምናሉ፡፡
2. **ገዳማትን ማእከል ያደረገ ሐዋርያዊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡**
   - ይህም ሲባል የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ትምህርትና ስልጠና ተባብረው ይቀርባሉ፤ የሚሰጡ ትምህርቶች እውቀት ነክ ብቻ እንዳይሆኑ ገዳማዊ ሕይወትንም በተግባር ከመለማመድ ጋር ያከናውናሉ፡፡

እኛ የምንቀስመው ልምድ (ቀጣይ)

3. **ጠንካራ የንስሐ አባት እና ልጅ ግንኙነት አለ፡፡**
   - ንስሃ አባቶችም ከንስሃ ልጆቻቸው በላይ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ዘርፈ ብዙ እውቀት እና ኢኮኖሚያዊ አቅም አላቸው (በእኛ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታየው ምእመናን ንስሃ አባቶቻቸውን በገንዘብ የሚደጉሙበት ሣይሆን ካህናቱ በገንዘብም የንስሃ ልጆቻቸውን ይደጉማሉ)፡፡
4. **ተደራሽ የስብከት ወንጌል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡**
   - የዘመኑን ቴክኖሎጂዎች በበርካታ አማራጮች ለምእመናኑ ያቀርባሉ፡፡
   - ለምሳሌ፡- **ከ15 በላይ የቴሌቪዝን ጣቢያዎች፤**
   - **ከ50 በላይ ድረገጾች፤**
   - እጅግ በርካታ **መንፈሳውያን መጽሐፍት፣ መጽሔት** እና **ጋዜጦች** በተለያዩ ቋንቋዎች፤ ወዘተ.

እኛ የምንቀስመው ልምድ (ቀጣይ)

5. **ለምእመናን የሚሰጡትን ማኅበራዊ አገልግሎቶች ከመንፈሳዊው ጋር እንደ ሥጋና ደም አዋሕደው ማስኬዳቸው**

—(አንድ ምእመን የዕለት ተዕለት ምድራዊ ኑሮው ከተቃወሰ መንፈሳዊውንም አጥብቆ ለመከታተል መቸገሩን ከመረዳታቸውም ባሻገር ወንጌላችንም ይህንን ጭምር ለሰዎች ማድረግ እንዳለብን ስለሚያዘን ነው)፤

6. **በተለይ ወጣቱን እና ሕጻናትን ማእከል ያደረገ አገልግሎት፡-**

– “the future of the Church is our youth……the future of our youth is the Church... it is indeed the future of the whole world.” “የቤተክርስቲያን ተስፋ ወጣቱ ነው። ….. የወጣቱ ብሎም የዓለምም የወደፊት ተስፋ ቤተክርስቲያን ናት)

7. **ድንበር አልባ አገልግሎት ፡**

• በራሳቸው ብቻ ሣይወሰኑ በተለያዩ የውጭ አገራት አርቶዶክሳዊት እምነትን ለማስፋፋት ጥናት ላይ የተመሰረተ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ያከናውናሉ፡፡

- የማላንካራ ቤተክርስቲያን ወንጌል ለማስፋፋት በየአካባቢዉ አብያተ ክርስትያናት አላት::
  - ለእነዚህ ቤተክርስቲያን እንደ አገልግሎቱ ስፋት **አንድ እና ከዚያ በላይ ካህናት በሀገረስብከቱ ሊቀጳጳስ አማካኝነት ይመደባሉ::**
  - ምዕመናኑ በሙሉ **በምሥጢረ ቁርባን የሚሳተፉ ሲሆን** ይህም ከካህናት ጋር ላላቸው ህብረት ማሳያ ይሆናል::
  - ከዚህም ባሻገር **ካህናቱ በሁለቱም በኩል የተሳሉ እንደመሆናቸው የማማከር አገልግሎትን ለወጣቶች፣ለሚያገቡ፣በአጠቃላይ ለምመናን በተናጥልና በጋራ በመሆን ይሰጣሉ::**
  - **ምዕመናኑም ከካህናቱ ጋር ያላቸው ቅርበት የአባትነትና የልጅን** ፈለግ የተከተለ መሆኑ እርስ በርስ ተቀራርበው ለመወያየት ዕድሉን ሰፊ አድርጎላቸዋል::

የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች

- በየአጥቢያዉ የሚገኙ ምዕመናን በየመንደራቸዉ ተከፋፍለዉ የራሳቸውን የመዝሙር ቡድን ሲኖራቸዉ በተለያዩ መርሐግብራት ላይ በተናጠል ወይም በጋራ ከህጻናት ከወጣቶች ጋር እናቶችና አባቶች በጋራ በመሆን መዝሙር ያቀርባሉ፡፡
- ከዚህም ባሻገር
  - መንፈሳው ትምህርት መማማር፣
  - ጸሎት በጋራ ማድረስ፣
  - አንዳንዴም በተናጠል ወላጆች ብቻ፣ እናቶች ብቻ በመሆን መንፈሳው ዝግጅት ማዘጋጀት እና መሳተፍ፤

የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች (ቀጣይ)

- በዙር ካህናት እየተመደቡ ቅዳሜ እና እሑድ በየመንደሩ በግለሰቦች ቤት መንፈሳዊ መርሐ ግብራትን ማዘጋጀት
- ሕዝቡ በሚሰማቸው ቋንቋዎች አገልግሎት መስጠት፡-
  - የማላንካራ ቤተክርሰስቲያን የአገልግሎት ቋንቋ የኬርላ ግዛት ቋንቋ በሆነዉ **ማልያለም** ሲሆን ከኬርላ ግዛት ውጪ የተወለዱ ቋንቋዉን የመናገር፤የመረዳት ችግር ስለሚገጥማቸዉ እነሱን ታሳቢ ባደረገ መልኩ **በወር እንድ ጊዜ እሁድ በእንግሊዘኛ** ወይም **ሂንዲ** ቋንቋ ቅዳሴ ይካሄዳል፡፡

የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች (ቀጣይ)

- **ዓለማዊ እንቅስቃሴዎችን በመንፈሳዊነት ቅኝት ማካሄድ**
  - ለምሳሌ የትልልቅ ምዕመናንን ልደት ያከብራሉ:: ለህጻናቱ በሰንበት ትምህርት ቤት ልደታቸዉ ፀሎት ተደርጎላቸዉ የሚከበርላቸዉ ሲሆን **አሥራሁለት ዓመት ሲሞላቸዉ በቅዳሴው ስርዓት ላይ ልዩ ፀሎት ተደርጎላቸዉ በቅድሚያ የሚቆርቡት እነሱ ይሆናሉ::**
- **በየቤተክርስቲያኑ በቅዳሴ ሰአት ምንጣፍ እንጅ ወንበር የሌላቸዉ ሲሆን** ይህም በአምላካችን ፊት ለፀሎት ስንቆም እንዴት እንቀመጣለን ከሚል የእምነት ጽናት የመጣ ነዉ::

የህንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮዎች (ቀጣይ)

- የቤተክርስቲያኗ ፀሐፊ እና የሰበካ ጉባኤ አባላት የሀገረስብከቱ ተወካዮች በተገኙበት በሚደረግ ምርጫ የሚመረጡ ሲሆን የአገልግሎት እንቅስቃሴያቸዉን እና የፋይናንስ ሪፖርት በየወሩ በግልጽ ቦታ ላይ (ቦርድ ላይ) የሚለጠፍ ሲሆን በየሶስት ወሩ በታተመ መጽሔት ለምዕመናኑ ይሰራጫል፡፡

ተሞክሮ አምስት

በልማት ሥራዎች

የሕንድ ቤተክርስቲያን በልማት ሥራዎች

- የህንድ ኦርቶዶክስ ምዕመናን ከአጠቃላይ የህንድ ህዝብ አንጻር ቁጥራቸው አነስተኛ **(2.5 ሚሊዮን)** ቢሆንም ከጥገኝነት ለመውጣት በሚያደርጉት ጥረት ለልማት ትልቅ ቦታ በመስጠት ይንቀሳቀሳሉ::
- በዚህም መነሻነት እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ራሳቸውን ለመቻል ከምዕመናን ከሚደረገው አስተዋጽኦ በዘለለ በትምህርት፣ በጤናና፣ በመሰረተ ልማት መስክ ተሰማርተው ይገኛሉ::
- የማላንካራን ቤተክርስቲያኝ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለየት የሚያደርጋት
  - የገነባችውን ህንጻ ከማከራት ይልቅ **ከአንደኛ ደረጃ ትምህረት እስከ ዩኒቨርሲቲ** በመክፈት፣ **ሆሲፒታሎችን** በመክፈት በራሷ ልጆች በማስተዳደር ሁሉም ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን እያደረገች መሆኗ ነው::









የማር ጎርጎርዮስ የክርስቲያን ተማሪዎች ህብረት (MGOCSM)

- የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሴሪያን ቤተክርስቲያን 110 ዓመት ያስቆጠረ መንፈሳዊ ማኅበር /የማር ጎርጎርዮስ የክርስቲያን ተማሪዎች ህብረት MGOCSM/ ሲኖራት መነሻዉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ ቢሆንም በአሁን ወቅት
  - ከፓትርያርኩ ጀምሮ ሊቃነጳጳሳትን፣
  - ካህናትንና
  - የሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ የህንድ ማላንካራ ቤተክርስቲያን ወጣቶች አባላት ናቸዉ::



NEWS & EVENTS

UNIT REGISTRATION 2019-2020

DOWNLOADS

STUDENT CENTRES / HOSTELS

Mar Gregorios Orthodox Christian Student Movement

MGOCSM, the 1st Spiritual sapling for students in Asia, is the spiritual organization of the Malankara Orthodox Syrian Church for its Student Community.

FIND OUT MORE

Need help? Contact us for more information.

ASK A QUESTION



የማር ጎርጎርዮስ የክርስቲያን ተማሪዎች ህብረት (MGOCSM)

- MGOCSM በመንፈሳዊ እና በልማት ሥራዎች የሚሳተፍ ሲሆን ከማኅበሩ አባልነት አንስቶ ሊቀጳጳስ የሆኑ ብዙዎች ሲሆኑ ለማሳያነት የአሁኑን **የማኅበሩን ፕሬዘዳንት አባ ቄርሎስን** መጥቀስ ይቻላል::
- ማኅበሩ በሀገር አቀፍ ደረጃና በአኅጉረ ስብከት ደረጃ ዓመታዊ አጠቃላይ ስብሰባዎችን ያደርጋል::
- የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሴሪያን ቤተክርስቲያን **ባሏት ሆስፒታሎች፤ ዩኒቨርሲቲዎች በአብዛኛዉ የሚያገለግሉት መነኮሳት፤ መነኮሳይት፤ ካህናትና ምዕመናን** ናቸዉ::
- ለምሳሌ ያህል **የካልካታው ሀገረስብከት ሊቀጳጳስ**
  - ጳጳስ ከመሆናቸዉ በፊት በኬርላ ዩኒቨርሲቲ

  የBioprocessing & Environmental science ፕሮፌሰር ነበሩ::



መንፈሳዊ ኮሌጆች

- የማላንካራ ቤተክርስትያን ካህናትን የሚያሰለጥኑ ሁለት ትልልቅ መንፈሳዊ ኮሌጆች ሲኖሯት

1. በኬርላ ግዛት ኮታይም ከተማ የሚገኘዉ **አልድ ሴሚናሪ** በኤዥያ ከሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት **200** ዓመት በማስቆጠር ቀዳሚው ሲሆን







መንፈሳዊ ኮሌጆች (ቀጣይ)

2. በማራሽትራ ግዛት ናግፑር ከተማ የሚገኘዉ **የቅዱስ ቶማስ መንፈሳዊ ኮሌጅ** ከኬርላ ግዛት ውጪ ለሚገኙ/ዲስፖራዎች/ምዕመናን ተደራሽ አገልግሎት እንዲሰጥ በ1995 እ.ኤ.አ የተቋቋመ ነዉ::

























Orthodox Theological Seminary, Kottayam
2016-20 Batch



የሕንድ ቤ.ክ የተለያዩ ተቀማት

- **የሕንድ ማላንካራ ቤተክርስቲያን**
  - **24 የአንድነት እና 12 የሴቶቸ ገዳማት/convents/፣**
  - **48 የሙት ልጆች መማሳደጊያ/orphanages/ ፣**
  - የሥጋደቄ/ለምጻሞች/ ተጠቂዎች ማረፊያ፤
  - በሱስ ተያዙ ወጣቶች ማገገሚያ ማዕከላት፣
  - የአረጋዉያን ማረፊያ ማዕከላት ሲኖራቸዉ
  - የተለያዩ ሀገረስብከቶች እንደየ አካባቢያዉ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ የበጎ አድራጎት ተቋማት ያላቸው ሲሆን በተጨማሪም የማኅበረሰቡን የዕለት ተዕለትኑሮ ለማሻሻል ከፍተኛ የሆነ ማኅበራዊ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

የሕንድ ቤ.ክ የተለያዩ ተቋማት

- ከመንፈሳዊ አገልግሎት ባሻገር የማላንካራ ቤተክርስቲያን
  - 22 ማተሚያ ቤቶች፤
  - 30 ሆስፒታሎች
  - 4 የኢንጅነሪንግ ትምህርት የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች፤
  - 52 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤
  - 10 የተማሪዎች ማረፊያ /ዶርሚተሪዎች/
  - በአጥቢያ የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች
  - በኤችአይቪ የተያዙ ሰዎች መጠለያ እና የመሳሰሉት ማእከላት አሏት።


M.O.S.C MEDICAL COLLEGE HOSPITAL
www.edubilla.com




M.O.S.C MEDICAL COLLEGE HOSPITAL





የሕንድ ቤ.ክ የተለያዩ ተቀማት

- በእነዚህ የአገልግሎት መስኮች በሁሉም ቦታ
  - የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች እንዲሳተፉ መደረጉና
  - በየአገልግሎት ዘርፉም አቅም የሌላቸው የቤተክርስቲያኒቱም ሆነ ሌሎች ሰዎች በነጻ እንዲጠቀሙ መደረጉ

በብዙ **አህዛብ ዘንድ የምትገኝ የለመለመች የበረሐ ተክል** እንድትሆንና **ተሰሚ እንድትሆን** አድርጓታል::

የሕንድ ቤ.ክ ገንዘብ አያያዝ

- **ቤተክርስቲያኒቷ**
  - **ከሙዳየ ምጽዋት አሰባሰብ** ጀምሮ ግልጽነት ያለው አሰራር በመከተሏ
  - በኢኮኖሚ ደረጃ ራሷን ከመቻል ባለፈ ችግረኞችን በመርዳት እና የካህናት ኑሮ ከምዕመኑ ያልተናነሰ እንዲሆን ማድረጓ
  - ካህናት ተረጋግው ተልኳቸውን እንዲወጡ ከማስቻሉም ባሻገር **ክህነት ስራ አጥተው የሚገቡበት ሳይሆን ሁሉ እያላቸው ለበለጠ ክብር የሚመርጡት መንፈሳዊ መንገድ** እንዲሆን አስችሏታል::
- በዚህም ምክንያት በህንድ አጥቢያ ቤተክርስትያን የሚለምኑ ምመናንን ማየት እንደ ብርቅ ነገር ሊቆጠር ይችላል::

ተሞክሮ ስድስት

የዘሙጉን የባሕል ወረራ መከላከል

የዘመኑን የባሕል ወረራ በተመለከተ

- በዚህ የሉላዊነት (Globalization) ዘመን በዓለም ሕዝቦች መካከል ከፍተኛ የባህል በወራረስ ይታያል፡፡
- ይህ የሚወራረሰው ባህል ግን መልካም ባህል ብቻ አይደለም፡፡ የዘመኑ ዓለማዊ እሳቤዎችና ኃጢአት እንደሥልጣኔ የሚቆጠርባቸው ባህሎችም መልካሞቹን ባህሎች እያበላሹ ይገኛሉ፡፡
- እኛ አቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ባህላችንን መጠበቅ ይገባናል፡፡ በዚህ ረገድ ሁሉም አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ ተግዳሮት ያለባቸው ሲሆን ይህን ለመከላከልም ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡
- በዚህ በኩል አብዛኛው ሥራ ማስተማር ነው፡፡ እነዚህ በላያቸው መልካም እና ነጻነት ያለባቸው የሚመስሉ ነገር ግን ውስጣቸው ኃጢአት የተጠናወታቸውን “ዘመናዊ” እንግዳ ባህሎች ለመከላከል ሁሉም አርቶዶክሳውያን እየጣሩ ይገኛሉ፡፡

ተሞክሮ ሰባት

የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን አጠቃቀም በተመለከተ

የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን አጠቃቀም በተመለከተ

- ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የዘመናችን መገለጫዎች ሆነዋል።
- በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው በአኗኗራችን ላይ አዎንታዊ መሻሻል ማምጣት የሚችሉ እና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳለጥ ሳይቀር ጥሩ መሳሪያዎች መሆን የሚችሉ ናቸው።
- በአግባቡ ካልተቀበልናቸው ደግሞ ወደ ስህተት መንገድ ሊወስዱ እና ለክፋት መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በዚህ በኩል ብዙ ልምድ ሊያሳዩን ይችላሉ።
  - የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመልካም ሥራ እና ለመንፈሳዊ አገልግሎት በብዛት እየተጠቀሙ ይገኛሉ።
  - ሌላውም ህዝብ ለበጎ እንዲጠቀም በተግባርም በትምህርትም ያበረታታሉ።
  - በአግባቡ ካልተቀበልናቸው ወደ ምን እንደሚወስዱ በሊቃውንቶቻቸው ጠለቅ ያለ ትንታኔ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

- የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከመጠቀም በተጨማሪ የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ክርስቲያናዊ እይታ ላይ በሚሠሯቸው ጥናቶች እና በሚሰጧቸው ትንታኔዎች ይታወቃሉ፡፡
  - ለዚህም በቅርቡ ያረፉት ሊቀ ጳጳስ ጳውሎስ ማር ጎርጎሪዮስ ተጠቃሽ ናቸው፡፡
  - እኒህ አባት የሳይንስ መሠረታዊ ፍልስፍናን ከኦርቶዶክሳዊ ክርስትና አንጻር በመተንተን ድንቅ ምልከታዎችን በጽሑፎቻቸው ጥለውልን አልፈዋል፡፡

የኢትዮያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም

- የኢትዮያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም የምታደርገው ጥረት እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ልምድ በመውሰድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እና ለቤተ ክርስቲያን እድገት በሰፊው መጠቀም ይኖርባታል።
- ምዕመናንም ስለ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ጤነኛ እይታ እንዲኖራቸው ማስተማር ይጠበቅባታል።
- የቤተ ክርስቲያኗን ሰ/ት/ቤቶችን ፣ ግቢ ጉባኤያትን ፣ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎችና የአብንት ት/ቤት ያሉ ደቀመዛሙርቶቻን ስለ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ጤነኛ እይታ እንዲኖራቸው እና ለመልካም ቢጠቀሙት የሚኖረውን ፋይዳ አስመልክቶ ተከታታይ ትምህርት መስጠት ይኖርባቸዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ.ክ ተሞክሮ ለሌሎች

- አስቀድመን በዝርዝር የተመለከትናቸው ተሞክሮዎች ማእከል ያደረጉት ‹‹ሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊያካፍሏት የሚችሉትን ተሞክሮዎች›› ነበር፤ በእርግጥም እነዚህ ሁሉ ልንማርባቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው::
- በአንጻሩ ደግሞ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ‹‹በምንም መልኩ ከሌሎች የማትሻል›› አድርጎ መግንዘብና አሉታዊ ሥዕል በአእምሮ ማስቀረት ተገቢ አይሆንም፤ የሌለንን ነገር ትኩረት ሰጥተን ብንፈልግ (ብንማር) የበለጠ እናድጋለን በሚል አስተሳሰብ እንጂ እኛም ያለን እጅግ በርካታ አዎንታዊ ነገሮች አሉና::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ.ክ ተሞክሮ ለሌሎች

- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ልታካፍላቸው የምትችላቸው ተሞክሮዎች በጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

1. በሥነ-ምግባር የተኮተኮቱ ልጆችን በተሻለ መልኩ የማፍራት እሴት ነበረን!
2. አብዛኛው ወጣቶቻችን ከሌሎች በተሻለ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱ እና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ናቸው፡፡
3. ምንም እንኳን ዛሬ ላይ የምናስተውለው ወጣት ቀይ መሥመሮችን የማለፍ አዝማሚያ ቢታይበትም አብዛኛው ማኅበረሰብ በክርስቲያናዊ እሴቶች (አመጋገብ፣ አለባበስ፣ አነጋገር እና መሰል የአኗኗር ዘይቤዎች) ላይ አለመደራደሩ መልካም ገጽታችን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በመላው ማኅበረሰብ ዘንድ ለሠረጸው ለዚህ አዎንታዊ እሴት ደግሞ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሚና የማይተካ ነው፡፡

አደረጃጀት እና መሪዎቻቸው

- የካህናት
- የህጻናት
- የሴቶች
- የወጣቶች
- የሰ/ት ቤቶች

የሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በረከት ይደርብን